የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፷፪
አዲስ አበባ ግንቦት ፲፭ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝቦች ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

17th Year No. 62
ADDIS ABABA 23rd May 2011


ማውጫ


ደንብ ቁጥር ፪፻፴፪/፪ሺ፫

የሀረማያ ዩኒቨርሲቲ እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ .......ገፅ ፭ሺ፰፻፸


CONTENTS


Regulation No. 232/2011

Haremaya University Re-establishment Council of Ministers Regulation ..................................... Page 5870


## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፴፪/፪ሺ፫

## ሀረሚያ ዩኒቨርሲቲን እንደገና ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፪ አንቀጽ ፭ እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩ አንቀጽ ፭(፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል ።

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የሀረማያ ዩኒቨርሲቲ እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፴፪./፪ሺ፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪. መቋቋም

፩) ሀረማያ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ እንደገና ተቋቁሟል።

፪) ዩዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል ።

፫) ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩ እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፲ /፪ሺ፫ መሠረት ይተዳደራል ።

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 232/2011

## COUNCIL OF MINISTER REGULATION TO PROVIDE FOR THE RE-ESTABLISHMENT OF THE HAREMAYA UNIVERSITY

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 5(1) of the Higher Education Proclamation No. 650/2009.

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as the "Haremaya University Re-establishment Council of Ministers Regulation No. 232/2011."

2. **Establishment**

1) The Haremaya University (hereinafter the "University") is hereby re-established as an autonomous higher education public institution having its own legal personality .

2) The University shall be accountable to the Ministry of Education.

3) The University shall be governed by the Higher Education Proclamation No. 650/2009 and the Federal Universities Council of Ministers Regulation No. 210./2011.


ያንዱ ዋጋ
Unit price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.Box 80,001

፫. <u>ዋና ግቢ</u>

የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ በሀረማያ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል ::

፬. <u>የተሻረ ደንብ</u>

የአለማያ ግብርና ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፺፰/፲፱፻፹፮ (በደንብ ቁጥር ፩፻፳፫/፲፱፻፺፰ እንደተሻሻለ) በዚህ ደንብ ተሽሯል ::

፭. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ::

አዲስ አበባ ግንቦት ፲፭ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ሚኒስትር

3. **<u>Main Campus</u>**

The University shall have its main campus at Haremaya and may establish elsewhere other academic units and centers of research and community services.

4. **<u>Repealed Regulation</u>**

The Alemaya University of Agriculture Establishment Council of Ministers Regulation No. 198/1994 (as amended by Regulation No. 123/2006) is hereby repealed.

5. **<u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 23rd day of May 2011.

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት